# የኢትዮጵያ ድምጽ ሬዲዮ መተዳደሪያ ደንብ

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያዊያን በተለያየ ምክንያት ወደ ስዊድን አገር መምጣት ከጀመርን ብዙ አመታት ተቆጥሯል። በተለይም ከአለፉት 20 ዓመታት ጀምሮ በፖለቲካ ችግር፣ በትዳር፣ በትምህርት እና በስራ ምክንያት ወደ ስዊድን እየመጣ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ቁጥሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ በጣም ከፍ እያለ መምጣቱ ሁላችንም የምናውቀው እውነታ ነው።አብዛኛውም ኢትዮጵያዊ በስዊድን ዋና ከተማ በስቶኮልም የሚኖር ሲሆን የቀረው ደግሞ በተለያዩ የስዊድን ከተማዎች ተበታትኖ የኖራል።

ምንም እንኳ የአመጣጣችን ምክንያት ይለያይ እንጂ በስዊድን በምንኖርበት ጊዜ በኢትዮጵያዊነታችን የሚያስተሳስሩን ብዙ የዜግነት መስተሳስሮች እንደ አሉን ምንም ጥርጥር የለውም። አንድ ቋንቋ ከመናገር እና የአንድ ባህል ተላባሾች ከመሆንም በአሻገር ችግሮቻችንም ሆኑ ደስታዎቻችን ከሞላ ጎደል ተመሳሳዮች ናቸውና። ኢትዮጵያውያን ከአገራችን ወጥተን ውጭ አገር በምንኖርበት ወቅት መተባበር፣ መገናኘትና ኢንፎርሜሽኖችን መለዋወጥ ከቻልን በኢትዮጵያውነታችን የሚደርሱብንን ችግሮች ሁሉ ለማቃለል እና እርስ በርስ ለመረዳዳት እንችላለን የሚል ጠንካራ እምነት አለን።

በተለይም ቁጥራችን እየጨመረ በመጣ ቁጥር በመሃላችን መኖር ያለበት የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ውስብስብ እየሆነ በመምጣቱ እና ለዚህም ችግር በመጠኑም ቢሆን ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል በመወሰን በስዊድን አካባቢ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን ሃሳብ የምንለዋወጥበት፣ የምንወያይበት፣ የዓለምንም ሆነ የሃገራችንን ጉዳዮች የምንከታተልበት አንድ ማዕከላዊ የመገናኛ ዘዴ በጥቂት ግለሰቦች አነሳሽነት በስውዲን ህግ በሚያዘው መሰረት አንድ የሎካል የሬድዮ ጣቢያ እንዲቋቋም ተደርጓል።

## 2. የድርጅቱ ስም

የድርጅቱ ስም " በስቶኮልም የኢትዮጵያ ድምጽ ሬድዮ" ተብሎ ተሰይሟል።

## 3. ዓላማ

ሬድዮው ከድርጅት፣ ከዘር እና ከሃይማኖት ተጽዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ በስዊድን ብሎም በአለም ዙሪያ ለምንገኝ ኢትዮጵያዊያን የ አገራችንም ሆነ የቀሪው የዓለም ዜናዎች፣ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች፣ መጠይቆች፣ ውይይቶችን እና የመሳሰሉትን የሚድያ ወጤቶች ያቀርባል።

## 4. የራዲዮው የፕሮግራም ይዘት

4.1. ምንጫቸው ሊጠቀስ ከሚችሉ የኢትዮጵያና አለም አቀፍ የዜና ምንጮች የሚገኙ ዜናዎችን ያቀርባል።

4.2. ከተለያዩ እና ከታወቁ ምንጮች የሚደርሱትን ዘገባዎች ትንተናዎችና ጥናቶችን ያስተላልፋል።

4.3. ህብረተሰቡን ሊያሰተምሩ የችላሉ ተብለው የሚገመቱ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ያቀርባል።

4.4. በአካባቢያችን በሚካሔዱና የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትንተና፣ ዜናዎችንና መረጃዎችን ያስተላልፋል።

4.5. የአገራችንን የተለያዩ ባህሎችን የሚያስተዋውቁና የሚያዳብሩ ልዩ ልዩ ባህላዊ ፕሮግራሞችን ያቀርባል።

4.6. በራዲዮው ፕሮግራም አማካኝነት አንድን ህዝብ ማንቋሸሽ ታሪኩን ማጉደፍ አንዱን ወገን በሌላው ወገን ላይ እንዲነሳ መቀስቀስ በጥብቅ ክልክል ነው።

4.7. ከአካባቢያችን ሆነ በሌላ ቦታ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች የሚያወጧቸውን መግለጫዎች እንደ አስፈላጊነቱ ይዘቱን ባልቀየረ መንገድ በማሳጠርና በመጥቀስ ለአድማጮች ያቀርባል። ሆኖም ግን በድርጅቶች መካከል በሚፈጠር ልዩነቶች ሳቢያ አንዱ ድርጅት በሌላው ላይ ዘለፋን ያዘለ ወይንም ስርአትን በዘለለ የጥላቻ ዘመቻ የሚያካሂድ መግለጫን ከማቅረብ ራዲዮው ይቆጠባል። ቀደም ሲል የተጠቀሰው አንቀጽ የሃሳብ ልዩነቶችን በጥሞና የሚያቀርቡ ልዩ ልዩ መግለጫዎችን የሚመለከት አይሆንም። ከማንኛውም ድርጅቶች በሬድዮ እንዲነበቡ የሚላኩ መግለጫዎች በተገቢው ተወካይ ፊርማ፣ በአድራሻና በማህተም የተደገፉ መሆን አለባቸው።

4.8. ከተቋቋሙም ሆነ ከሚቋቋሙ ኢትዮጵያዊያን ድርጅቶች ለኢትዮጵያዊያን የሚያደርጉ ጥሪዎች የስብሰባ ወይም የምሽት ማስታወቂያዎች በራዲዮው ሊተላለፍ ይችላል።
4.9. ራዲዮው በሚያስተላልፋቸው ፕሮግራሞች የስዊድንን የ Narradio ህግ ተከትሎ ይሰራል።
4.10. ሌሎችም ከ Narradio ህግ ውጭ ያሉትም ለምሳሌ ያህል የመናገር እና የመጻፍ ነጻነት የሚከበሩ ይሆናል።
4.11. ራዲዮው  ይህን ህገ ማህበር የማይቃረን እና የስዊድንን ህግ የማይጥስ ማንኛውንም ትምህርታዊ እና ጠቃሚ የሆኑ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት ይቻላል።
4.12. ለታፈኑ ለዲሞክራሲ እና ለሰበአዊ መብት ታጋዮች መድረክ በመፍጠር ሀሳባቸው እንዲሰማ እድል ይሰጣል።
4.13. ህዝብ የማወቅ መብት አለው የሚለውን የሬድዮኑን አላማ ለማስፈጸም ይጥራል።

## 5. አባልነት

5.1. ማንኛውም በስዊድን ነዋሪ የሆነ እና የሬድዬውን ህገ ማህበር የተቀበለ ግለሰብ አባል መሆን ይችላል።
5.2. አንድ አባል መብቱ በትክክል የሚጠበቀው በጠቅላላ ጉባኤው የተወሰነውን የአባልነት መዋጮ በየዓመቱ በከፈለ ግዜ ብቻ ይሆናል።

## 6. የራድዮው የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ

6.1. የራድዮው የስራ አስኪያጅ አባላት ቁጥር 5 ይሆናል።
6.2. የስራ አስኪያጅ ኮሚቴው በሁለት አመት አንዴ በጠቅላላ ጉባኤው ይመረጣል።

## 7. የራድዮው የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተግባራት

7.1. ራድዮውኑ በስዊድን ህግና በራድዮው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መስራቱን ይቆጣጠራል።

7.2. በአጠቃላይ ለራድዮው ፕሮግራም መመሪያ እና ፖሊሲ እንዲሁም በጀትና የሰራ እቅድ ይነድፋል።
7.3. ኮሚቴው ቢያንስ በሶስት ወር አንዴ ይሰበሰባል። በስብሰባውም ወቀት ያለፉትን ወራት ይገመግማል። ችግርም ከአለ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።
7.4. ከግለሰብ አድማጮች ወይም ከድርጅቶች በራድዮው ፕሮግራም ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎቸን ወይንም ክሶችን ይመረምራል መፍትሄም ይፈልጋል።
7.5. የሬድዮኑን ዋና አዘጋጅና ተጠባባቂ አዘጋጅ ከዝግጅቱ ክፍሉ ጋር በመሆን ይመርጣል።
7.6. የኮሚቴው የስራ ዘመን ሁለት አመት ነው።
7.7. የራድዮው የገንዘብ ሃይል የሚጠናከርበትን መንገዶች በማጥናት ገንዘብ ያሰባስባል።
7.8. የሬድዮውን አላማ በማስረገጥ ቀስቀሳ የደርጋል።
7.9. ሬድዮኑን ለማጠናከር አባላትን ይመለምላል፤ አባላት የአባላት መዋጮ መክፈላቸውንም ያረጋግጠል።

# 8. የሬድዮ ስራ አስኪያጅ አባላት የስራ ክፍፍል

## 8.1. ሊቀመንበር

8.1.1.የኮሚቴውን ስብሰባዎች ይመራል
8.1.2.የራድዮው ስራ በትክክል መካሄዱን ከሌሎች የኮሚቴው አባላት ጋር በመሆን ይቆጣጠራል።
8.1.3.ማህበሩን በመወከል አስፈላጊ የሆኑትን ግንኙነቶች ያደርጋል።
8.1.4.የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያና ውሳኔዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል።
8.1.5.ከገንዘብ ያዥ ጋር በመሆን ገንዘብ ፈርሞ ያወጣል። የሬድዮኑን ንብረቶች ይጠብቃል ተመዝግበው መያዛቸውንም ይቆጣጠራል።

## 8.2. ምክትል ሊቀመንበር

8.2.1. ለቀምንበሩ በሌለበት ወቅት የሊቀመንበሩን ቦታ በመተካት የሊቀመንበሩን ሀላፊነት በሙሉ በመውሰድ ይሰራል።
8.2.2. የማህበሩም ማለትም የሬድዮው የድረጅት ጉዳይ ሀላፊነትንም ደርቦ ይሰራል። ይህም ማለት በተለይ የ አባላት ምልመላ እና ምዝገባ ጉዳይ የምክትል ሊቀመንበሩ የስራ ሀላፊነት ይሆናል።

## 8.3. ፀሃፊ

8.3.1. የስብሰባዎችን አጀንዳ ከሊቀመንበሩ ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤ ቃለ ጉባዔም ይይዛል።
8.3.2. በራድዮው የሚተላለፉትን ዜናዎች፣ የፁሁፍ ዶክሜንቶችና ማስታወቂያዎች እንዲሁም የስራ እና የሂሳብ ሪፖረቶች መዝግቦ ያስቀምጣል። በተጠየቀም ግዜ ያቀርባል።
8.3.3. ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር የቦርዱን ስብሰባዎች ይጠራል።
8.3.4. በውሳኔ መሰረት ደብዳቤ ይጽፋል፤ መጪ ደብዳቤውችን መዝግቦ ይይዛል።

## 8.4. ገንዘብ ያዥ

8.4.1. የራድዮኑን ገንዘብና ንብረት በጥንቃቄ መዝግቦ ይይዛል።
8.4.2. ከሊቀመንበሩ ጋር በመሆን ከራድዮው የሂሳብ ቁጥር ገንዘብ ያወጣል። ክፍያዎች እና ገቢዎችን ይቆጣጠራል። በትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መርሆም መዝግቦ ይይዛል።
8.4.3. በየጊዜው የወጪ እና የገቢ ዝርዝር በመሰራት የሬድዮኑን ሂሳብ ያመሳክራል። የሂሳብ ሪፖርትም ያቀርባል።

### 8.5. የህዝብ ግኑኝነት ሀላፊ

8.5.1. የራድዮኑን አላማ ለህዝብ የስተዋውቃል።
8.5.2. እንደ አስፈላጊነቱ ሬድዮኑን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች ለህበረተሰቡ መልስ ይሰጣል።
8.5.3. በ አጠቃላይ በሬድዮኑ እና በአድማጮቹ መሀል መልካም ግኑኝነት እንዲፈጠር እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል።

## 9. ኦዲተር

9.1. አንድ ኦዲተር ከስራ አስኪያጁ ጋር በሁለት ዐመት አንድ ግዜ በጠቅላላ ጉባኤው ይመረጣል።
9.2. ኦዲተሩ በየአመቱ አንድ ጊዜ ስራ አስኪያጁ የማህበሩ ህገ ደንብ እና የስዊድንን ህግ በተከተለ መስራቱን ጥናት በማድረግ ሪፖረት ለአባላት ያቀርባል።
9.3. በየአመቱ ለጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩን የሂሳብ ሪፖረቱ በተመለከተ ሪፐረት የቀርባል።

## 10. የራድዮው ዝግጅት ክፍል

10.1. የራድዮው ዝግጅት ክፍል ዋና አዘጋጅና ተጠባባቂ አዛጋጅ ይኖረዋል።
10.2. የራድዮው ዝግጅት ክፍል በዋና አዘጋጅውና በተጠባባቂ አዛጋጅው የሚመራ ልዩ ልዩ ፕሮግራም አዘጋጅዎች ይኖሩታል።
10.3. የራድዮው ዝግጅት ክፍል የስራ ጊዜ ሁለት ዓመት የሆናል።

### 10.1. የራድዮው ዋና አዘጋጅ

10.1.1. በስዊድን ህግ መሰረት ዋና አዘጋጅው በራድዮው በሚተላለፉት ፕሮግራሞችበሙሉ ተጠያቂ ነው።
10.1.2. ዋና አዘጋጁ በተጓዳኝነት ለስራ አስኪያጁም ተጠያቂነት ይኖርበታል።

10.1.3. ያለ ዋናው አዘጋጅ ፈቃድ በራድዮው ምንም አይነት ፕሮግራም ማስተላለፍ በጥበቅ የተከለከለ ነው።

10.1.4. ዋና አዘጋጁ በራድዮው የሚተላለፉትን ፕሮግራሞች በመመዝገብ መያዛቸውን ይቆጣጠራል ያረጋግጠልም።

## 10.2. ተጠባባቂ ዋና አዘጋጅ

10.2.1. የራድዮው ዋና አዘጋጅ በሌለበት ወቅት የዋና አዘጋጅውን ሃፊነትና ግዴታ በሙሉ ይረከባል።

10.1.2. ተጠባባቂ ዋና አዘጋጅው የራድዮኑን ሃላፊነት ተረክቦ በሚያስተላልፈበት ወቅት የቀኑን ፕሮግራም አዘጋጅ መሆኑን ስሙን በመጥቀስ በራድዮው መግለጽ ይኖርበታል።

## 11. አመታዊ ስብሰባ

11.1. ምንም እንኳን የዝግጅት ክፍሉ እና የስራ አስኪያጅ ኮሚቴው የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ቢሆንም በአመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤ ይደረጋል።

11.2. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አመቱን ሳይጠብቅ ጠቅላላ ጉባኤው በ አስቸኳይ ሊጠራ ይችላል። ይህም ተገባሪ የሚሆነው ግማሽ ወይንም ከግማሽ በላይ የሚሆነው አባል ፍላጎቱ ከሆነ ወይንም ደግሞ ስራ አስክያጁ በራሱ ስበሰባ መጠራቱን ከ አመነበት ይሆናል።

## 12. የአመታዊ ስብሰባ ተግባራት

12.1. ጠቅላላ ጉባኤው ሊኪያሄድ የሚችለው ከአባላቱ ሀምሳ በመቶ ሲገኝ ብቻ ነው።

12.2. አመታዊ ስብሰባው በስራ አስኪያጅ ኮሚቴው በኩል የሚያቀርበውን የስራ ሪፖረት፣ የሂሳብ ሪፖርት እና የኦዲተር ሪፖርት አዳምጦ ውሳኔ ይሰጣል።

12.3. የራድዮኑን ሂደት በመገምገም ለሚቀጥለው አመት ማሻሻያዎችን፣ ለውጦችንና መመሪያዎችን ለስራ አስኪያጁ ይሰጣል።

12.4. በሁለት አመት አንዴ  የስራ አስኪያጅ አባላትን ይመርጣል።
12.5. በሁለት አመት አንዴ አንድ ኦዲተር ይመርጣል።
12.6. በአመታዊ ስብሰባ ላይ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ተግባራዊነት የሚኖራቸው ከተሰበሰቡት አባላት ከመቶ ሰባ በላይ ከደገፏቸው ብቻ ይሆናል። ሆኖም ግን ይህ የድምፅ አሰጣጥ የድርጅቱን መፍረስ በሚመለከት ስራ ላይ አይውልም።

## 13. የህገ ማህበር ማሻሻል

13.1. አባላት እንዲሻሻሉ የሚፈልጓቸው አንቀፆች ካሉ ወይም ጠቅላላ የህግ ማህበሩን ማሻሻልን ከጠየቁ የስራ አስኪያጁ አባላት ጥያቄውን በማጤን ረቂቅ ሃሳብ ለአመታዊ ስብሰባው በማቅረብ የህገ ማህበሩን መሻሻል ይጠይቃሉ።
13.2. ይህ ህገ ማህበር የሚሻሻለው አመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ የህገ ማህበሩን መሻሻል ከጠየቀና በስብሰባው ከተገኙት አባላት ከመቶ ሰባ ከደገፉት ይሆናል።

## 14. የድርጅቱ መፍረስ

14.1. በተለያዩ ምክንያቶች የድርጅቱ መፍረስ ጥያቄ ከተነሳ ድርጅቱ መፍረስ የሚችለው ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ከአባላት ሃምሳ በመቶ ተገኝተው ከተገኙት አባላት ከመቶ ሰማንያ መፍረሱን ከደገፉት ብቻ ይሆናል።
14.2. የድርጅቱ መፍረስ ከተወሰነ የድርጅቱ ንብረት ለማን እንደሚተላለፍና ለምን አላማ እንደሚውል የተሰበሰቡት አባላት በድምፅ ብልጫ ይወስናሉ። አባላት መሰብሰብ ካልቻሉ የድርጅቱ ንብረት ተመሳሳይ አላማ ላለው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ይተላለፋል። ለዚህም ተፈጻሚነት የስራ አስኪያጁ ሀላፊነት ይሆናል።